# መመሪያ ቁጥር 1065/2017
# የዕጽዋት ዝርያ ለቀቃ እና ምዝገባ መመሪያ

# Directive No. 1065/2025
# Plant Variety Release and Registration Directive

| የዕጽዋት ዝርያ ለቀቃ እና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 1065 /2017 | Plant Variety Release and Registration Directive Number 1065 /2025 |
|---|---|

የዕፅዋት ዝርያ ለቀቃ እና ምዝገባ ሥርዓት በመዘርጋት ኢትዮጵያ ከዘርፉ የምታገኘውን ጠቀሜታ ለማሳደግ እንዲሁም በቀጠናዊና ዓለም አቀፍ ደረጃ እየተተገበሩ ካሉ የዕፅዋት ዝርያ ለቀቃ እና ምዝገባ ሥርዓት ጋር በማጣጣም የዘርፉን ተወዳዳሪነትና ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የግብርና ሚኒስቴር በዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 1288/2015 አንቀጽ 4(1)፣ 4(8)(መ) እና 29(2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

Whereas it is necessary for Ethiopia to increase the benefits from the seed sector through harmonization of regional and international plant variety release and registration practices that leverages market competitiveness, the Ministry of Agriculture based on Seed Proclamation No. 1288/2023 article 4(1), 4(8)(d), and 29(2) has issued this directive.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

## Section One
## General

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ “**የዕፅዋት ዝርያ ለቀቃ እና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 1065/2017**” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**1.** **<u>Sort Title</u>**

This directive may be cited as **‘‘Plant Variety Release and Registration Directive No. 1065/2025’’**.

## 2. ትርጉም

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የማያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"አመልካች"** ማለት የዕፅዋት ዝርያ እንዲለቀቅለት ወይም እንዲመዘገብለት ወይም በልዩ ፍቃድ የዕፅዋት ዝርያ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ለባለስልጣኑ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ነው፣
2) **"ብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ"** ማለት በባለስልጣኑ የሚቋቋም በዕጩ እና ከመመረት ውጭ በሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎች ላይ ውሳኔ የሚሰጥ ገለልተኛ ኮሚቴ ነው፣
3) **"የዕጩ ዝርያዎችን ብቃት የሚገመግም ቴክኒካል ኮሚቴ"** ማለት በባለስልጣኑ የሚቋቋም የዕጩ ዝርያዎችን ብቃት እና የባህርይ ልየታ ፍተሻ የሚገመግም ገለልተኛ ቴክኒካል ኮሚቴ ነው፣
4) **"ከመመረት ውጭ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎችን የሚገመግም ቴክኒካል ኮሚቴ"** ማለት በባለስልጣኑ የሚቋቋም የዕፅዋት ዝርያዎችን ከመመረት ውጭ መሆን ስላለባቸው የሚገመግም ገለልተኛ ቴክኒካል ኮሚቴ ነው፣

## 2. Definition

In this directive, unless otherwise a different meaning is given:

1/ **"Applicant"** means a person who applies for the release or registration of plant variety or for importing plant variety through a special permit''.
2/ **''National variety release committee"** means a neutral committee established by the Authority with the responsibility of deciding on plant variety release, registration and on varieties that become obsolete and require decision.
3/ **"Candidate variety evaluating technical committee''** means a neutral technical committee established by the Authority to evaluate the performance and distinctness, uniformity and stability test of candidate varieties.
4/ **''Obsolete variety evaluating technical committee''** means a committee established by the Authority to evaluate varieties that become obsolete and need decision.

5) **"ዕጩ የዕፅዋት ዝርያ"** ማለት በአመልካች እንዲለቀቅ እና እንዲመዘገብ ለባለስልጣኑ ጥያቄ የሚቀርብበት ነው፣

6) **"ከመመረት ውጭ የሆነ የዕፅዋት ዝርያ"** ማለት በተለያየ ምክንያት ከመደበኛው የዘር ብዜት ሥርዓት ውጭ እንዲሆን የሚደረግ የዕፅዋት ዝርያ ማለት ነው፣

7) **"ያልተመዘገበ ዝርያ"** ማለት በሀገሪቱ የዕፅዋት ዝርያ መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ ያልሰፈረ ዝርያ ማለት ነው፣

8) **"የተገለለ ግብርና"** ማለት ተለይቶ በሚታወቅ አካባቢ በዘር ምክንያት አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳይፈጠር በባለስልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር የሚካሄድ ግብርና ነው።

9) **"አዋጅ"** ማለት የዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 1288/2015 ነው፣

5/ **''Candidate variety''** means a variety submitted to the Authority by the applicant for release and registration.

6/ **''Obsolete variety"** means a variety which has become unfit to be produced in the regular seed multiplication system due to various reasons.

7/ **''Unregistered variety''** means variety not registered in the national variety register book of the country.

8/ **''Protected agriculture''** means a secluded production area identified and controlled by the Authority for reasons of negative impact on seed.

9/ **"Proclamation"** means plant seed proclamation No. 1288/2023.

## ክፍል ሁለት

## ዝርያ ስለመልቀቅና መመዝገብ

### 3. ዕጩ ዝርያ ሰለመልቀቅ

1) አንድ ዕጩ ዝርያ ከመለቀቁ በፊት የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ እና የባህሪ ልየታ ፍተሻ ሊደረግለት ይገባል፤

2) እንደየዕፅዋት ዓይነቴዎች የዕጩ ዝርያ ብቃት ማረጋገጫ፣ የባህሪ ልየታ ፍተሻ እና የማላመድ ሙከራ በባለስልጣኑ ወይም በአመልካቹ ሊሰራ ይችላል፤

3) አስቀድሞ በውጪ ሀገር የተመዘገበ ዝርያ በሀገር ውስጥ ለማስመዝገብ በውጪ ሀገር ዕውቅና ባለው ተቆጣጣሪ አካል የተሰራ የባህሪ ልየታ ፍተሻ ሪፖርት እና በአመልካቹ የተሰራ የማላመድ ሙከራ መቅረብ አለበት፣

4) ለእያንዳንዱ የሰብል አይነቴዎች ዝርዝር የአመዘጋገብ ሂደቶች፣ የባህሪ ልየታ ፍተሻ፣ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ ሙከራ እና የማላመድ ሙከራ በየሰብሉ ዓይነት በሚዘጋጁ የቴክኒካል ፕሮቶኮሎች መሰረት ይሆናል፡፡

## Section Two

## Variety Release and Registration

### 3. Release of candidate variety

1/ A candidate variety must undergo national performance trial and disticintness, uniformity and stability test prior to release.

2/ Depending on the type of plant species, the national performance trial, the disticintness, uniformity and stability test and adaptation trial of the candidate varieties shall be done by the Authority or by the applicant.

3/ In order to register a variety already registered abroad, a distinctness uniformity and stability test report made by a foreign recognized regulatory body and adaptation trial made by the applicant must be submitted.

4/ The distinctness, uniformity and stability test, national performance trial and adaptation trial shall be done in accordance with the technical protocols to be prepared for each of the crop species.

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ከ1 - 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በባለስልጣኑ ልዩ ሀገራዊ ፋይዳ መኖሩ ሲረጋገጥ ወይም ዝርያው መልሶ ተባዝቶ ወደ ውጪ ለመላክ ዓላማ ሲጠየቅ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ እና የባህሪ ልየታ ፍተሻ ማድረግ ሳያስፈልግ በውጪ ሀገር ተመዝግበው በሀገር ውስጥ ላልተመዘገቡ ዝርያዎች በቀጥታ እንዲመረቱ ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

5/ Subject to the provisions of sub article 1- 4 of this article, when it is confirmed by the Authority that there is a special national interest and the variety is requested for export porpose, direct production permission shall be given to the variety, which is registered abroad but not registered in the country, without the need of conducting national performance trial and distinctness, uniformity and stability test.

**4. በባለስልጣኑ ስለሚሰሩ የዕፅዋት ዓይነቴዎች የዕጩ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ እና የባህሪ ልየታ ፍተሻ**

**4. For plant species where distinctness, uniformity and stability test and the national performance trial done by the Authority**

1) አመልካቹ በዕጩ ዝርያ መፈተሻ ፕሮቶኮል በተገለጸው መሰረት ከተፈላጊ የዘር መጠን ጋር ባለስልጣኑ ባዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ተገቢውን ክፍያ በመክፈል፡-

ሀ) ለመኸር ወቅት ሙከራ ከሆነ ከየካቲት 1 እስከ መጋቢት 30 እንዲሁም ለበልግና ለመስኖ ሙከራ ከሆነ ደግሞ ከነሐሴ 1 እስከ መስከረም 30 ማመልከት አለበት፣

1/ The applicant shall apply using an application form prepared by the Authority along with the appropriate service fee and the required amount of seeds as specified in the candidate varieties testing protocol:-

a) If the test is for ‘Meher’ season, from February 1st to March 30th, and if it is for irrigation and ‘Belg’ season, from August 1st to September 30th.

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለደንና ለሌሎች ቋሚ ሰብሎች ለየት ያለ የአየር ንብረት ላላቸው አካባቢዎች ሲሆን ግን በማንኛውም ወቅት ማመልከት ይችላል፣

2) ዝርያው ከውጭ ሀገር የሚገባ ከሆነ አስፈላጊው የኳራንቲንና የብዝሃ ህይወት መስፈርት ሟሟላትና ልውጥ ህያው አለመሆኑን፤ ከሆነም አግባብ ካለው ተቋም የተፈቀደ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ማስረጃ አመልካቹ ማቅረብ አለበት።

3) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ እንቀፅ1 መሰረት የቀረበለትን ማመልከቻ በመመርመር በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፣

4) ባለስልጣኑ የቀረበውን ማመልከቻ የተቀበለ ከሆነ

ሀ) በዕጩ ዝርያ መፈተሻ ፕሮቶኮል መሰረት ምስጢራዊነቱን በጠበቀ መልኩ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ እና የባህሪ ልየታ ፍተሻ ሙከራ ለሁለት ተከታታይ ዓመት እንዲካሄድ ያደርጋል፣

b) Without prejudice to this article sub articile 1(a), for forest and other perennial crops having peculiar climate conditions, application may be submitted at any time of the year.

2/ The applicant needs to ensure the variety fulfills the plant quarantine and biodiversity requirements, if the variety is from foreign sources, and should declare whether the variety is genetically modified organism or non- genetically modified organism; if it is genetically modified organism, evidence of permit from the appropriate institution must be submitted to the Authority.

3/ The Authorithy reviews the application recived based on sub article 1 of this article and informs its decision to the applicant within 15 days.

4/ If the Authority accepts the submitted application

a) According to the candidate variety testing protocol, will carry out the the national performance trial and the distinctness, uniformity and stability test for two consucative years in a confidential manner;

ለ) በዕጩ ዝርያ ብቃት ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ አማካኝነት ሙከራው በሁለተኛው ዓመት እንዲገመገም ያደርጋል፣

ሐ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4/ሀ እና ለ የተደነገገው ቢኖርም የደንና ለሌሎች ቋሚ ሰብሎች የሙከራና የመገምገሚያ ጊዜ እንደየእጽዋቱ የመገምገሚያ ፕሮቶኮል መሰረት የሚወሰን ይሆናል፣

5) የመጀመሪያ የምርት ወቅት ሙከራ ሲጠናቀቅ ውጤቱን ለአመልካቹ እና ለዕጩ ዝርያ ብቃት ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

6) ሙከራው ሲጠናቀቅ ከዕጩ ዝርያ ብቃት ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ የግምገማ ሪፖርት በጽሁፍ ይቀበላል፣

7) ከዕጩ ዝርያ ብቃት ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ በቀረበለት ሪፖርት መሰረት በብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፣ ውሳኔውንም ለአመልካቹ ያሳውቃል።

**5. በአመልካቹ ስለሚሰሩ የዕጩ ዝርያ ብቃት ማረጋገጫ ወይም የማላመድ ሙከራ ወይም የባህርይ ልየታ ፍተሻ**

b) Have the trial evaluated in the second year by the candidate variety evaluating technical committee.

c) Without prejudice to this article sub article 4(a) and (b), the testing and evaluation period for forest and other plants shall be determined according to the evaluation protocol of each plant.

5/ Upon completion of the first production season test, the results shall be communicated to the applicant and the candidate's variety evaluating technical committee.

6/ At the end of the trial, the Authority will receive a written evaluation report from the candidate variety evaluating technical committee.

7/ Based on the report of the candidate variety evaluating technical committee, makes a decision by the national variety release committee, and notifies the decision to the applicant.

**5. The national performance trial or adaptability trial or distinctness, uniformity and stability test of the candidate variety done by the applicant**

1) አመልካቹ በራሱ የዕጩ ዝርያ ብቃት ማረጋገጫ ወይም የማላመድ ሙከራ ወይም የባህሪ ልየታ ፍተሻ ለማሰራት፡-

ሀ) የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ለመኸር ወቅት ሙከራ ከሆነ ከየካቲት 1 እስከ መጋቢት 30 ለበልግና ለመስኖ ሙከራ ከነሐሴ 1 እስከ መስከረም 30 ማመልከት አለበት፣

ለ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለደንና ለሌሎች ቋሚ ሰብሎች ወይም ለየት ያለ የአየር ንብረት ላላቸው አካባቢዎች በማንኛውም ወቅት ማመልከቻውን ማቅረብ ይቻላል፣

ሐ) ዝርያው ከውጭ ሀገር የሚገባ ከሆነ ከማመልከቻው ጋር ዝርያው አስፈላጊው የኳራንቲንና የብዝሃ ህይወት መስፈርት ሚሟላቱንና ልውጥ ህያው አለመሆኑን ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፤ ዝርያው ልውጥ ህያው ከሆነም አግባብ ካለው ተቋም የተፈቀደ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣

1/ To conduct the national performance, the distinctness, uniformity and stability test and the adaptation trial by the applicant himself:-

a) The applicant shall apply from February 1st to March 30th, if the test is for 'Meher' season, and from August 1st to September 30th if it is for irrigation and 'Belg' season with appropriate service fee;

b) Without prejudice to this article sub articile 1(a), for forest and other perennial crops having peculiar climate conditions, application may be submitted at any time of the year.

c) The applicant needs to ensure the variety fulfills the plant quarantine and biodiversity requirements, if the variety is from foreign sources, and should declare whether the variety is genetically modified oorganism or non- genetically modified oorganism; if it is genetically modified organism, evidence of permit from the appropriate institution must be submitted to the Authority.

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የቀረበለትን ማመልከቻ በመመርመር ባለስልጣኑ፡-

ሀ) በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለአመልካች ማሳወቅ አለበት፣

ለ) የቀረበውን ጥያቄው ከተቀበለው አመልካች ለሙከራ የሚሆን ዘር ከውጭ የሚያስገባ ከሆነ የማስገቢያ ፍቃድ ይሰጣል፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) መሰረት ፍቃድ ያገኘ አመልካች የዕጩ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫውን ወይም የባህርይ ልየታ ፍተሻውን ወይም የማላመድ ሙከራውን

ሀ) ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ፕሮቶኮል መሰረት ማከናወን አለበት፣

ለ) በዕጩ ዝርያ ብቃት ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ እንዲገመገምለት ከ15 ቀናት በፊት ባለስልጣኑን መጠየቅ አለበት፣

ሐ) የምርት ወቅት ሙከራ ሲጠናቀቅ ውጤቱን ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት።

4) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3(ለ) መሰረት ጥያቄ ሲቀርብለት በዝርያ ብቃት መገምገሚያ ፕሮቶኮል መሰረት

2/ After evaluating the application submitted according to sub-article 1 of this article, the Authority:-

a) Informs the applicant the decision within 15 days.

b) If accepts the applicant’s request, and if the variety is imported, will issue an import permit of seeds for testing purpose.

3/ If the applicant get permission to conduct the candidate variety national performance trial or distinctness, uniformity and stability test or adaptation trial according to sub article of 2 (b) of this article, the applicant shall

a) Conduct according to the protocol prepared by the Authority;
b) Request the Authority 15 days in advance to be evaluated by the candidate variety evaluating technical committee;
c) Report the trial result to the Authority on completion of production period.

4/ When the Authority is requested according to sub-articile 3(b) of this article, assign the candidate variety evaluating technical committee for

ዕጩ ዝርያው በዝርያ ብቃት ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ አማካኝነት ሙከራው እንዲገመገም በማድረግ ሪፖርት መቀበል አለበት፣

5) የዕጩ ዝርያ ብቃት ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ ባቀረበለት ሪፖርት መሰረት ባለስልጣኑ በብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ ውሳኔውንም ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት።

6. **ከውጭ ሀገር የተመዘገበ ዝርያ አስገብቶ በሀገር ውስጥ የማላመድ ሙከራን በማካሄድ ዝርያ ስለመመዝገብ**

1) በውጭ ሀገር የተመዘገብ ዝርያ በሀገር ውስጥ የማላመድ ሙከራን በማካሄድ ሊመዘገብ ይችላል፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት በውጭ ሀገር የተመዘገበ ዝርያን ከመመዝገቡ በፊት አምልካቹ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ሊያሟላ ይገባል፡-

ሀ) ባለስልጣኑ ባዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ መሰረት

evaluation and recive report that has been done according to the protocol.

5/ Based on the report of the candidate variety evaluating technical committee, makes a decision by the national variety release committee, and notifies the decision to the applicant.

5) **Registering a variety by importing a registered variety, and conducting adaptability trial**

1/ A variety registered abroad may register through conducting adaptation trial.

2/ According to sub article 1 of this article, an applicant should fulfill the following precondiations to register a variety registered abroad:-

a) The applicant shall apply from April 1st to May 30th, or from August 1st to September 30th using the application form provided by the Authority along with the appropriate service fee.

ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ከሚያዝያ 1 እስከ ግንቦት 30 ወይም ከነሐሴ 1 እስከ መስከረም 30 ማመልከት፣

ለ) በውጭ ሀገር እውቅና ካለው ተቆጣጣሪ አካል የዝርያ የባህሪ ልየታ ፍተሻ ማስረጃ ለባለስልጣኑ ማቅረብ፣

ሐ) አስፈላጊውን የኳራንቲንና የብዝሃ ህይወት መስፈርት ሚሟላትና ልውጥ ህያው አለመሆኑን ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፤ ዝርያው ልውጥ ህያው ከሆነም አግባብ ካለው ተቋም የተፈቀደ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ፣

3) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የቀረበለትን ማመልከቻ እና ማስረጃ በመመርመር

ሀ) በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለአመልካች ያሳውቃል፣

ለ) ጥያቄውን ከተቀበለው አመልካች ለማላመድ ሙከራ የሚሆን ዘር ማስገባት እንዲችል የማስገቢያ ፍቃድ ይሰጣል፣

b) Shall submit a report a recognized abroad regulatory body on the distinctness, uniformity and stability of the variety to the Authority.

c) The applicant needs to ensure the variety fulfills the plant quarantine and biodiversity requirements, if the variety is from foreign sources, and should declare whether the variety is genetically modified oorganism or non- genetically modified oorganism; if it is genetically modified organism, evidence of permit from the appropriate institution must be submitted to the Authority.

3/ According to sub article 2 of this article, after examing the application and evidence submited the Authority shall:-

a) Inform the applicant of the decision within 15 days;

b) If accepts the applicant’s request, will issue an import permit of seeds for adaptation trial purpose.

ሐ) በአመልካቹ የቀረበውን መረጃ ተቀብሎ ዝርያው ጥቅም ላይ እንዲውል ይፈቅዳል

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3(ለ) መሰረት የማስገቢያ ፍቃድ የተሰጠው አመልካች፡-

ሀ) ባለስልጣኑ ባዘጋጀው የዝርያ የማላመድ ሙከራ ፕሮቶኮል መሰረት ሙከራውን ማከናወን እና፣

ለ) በዝርያው ላይ በሀገር ውስጥ የተሰራ የዝርያ ማላመድ ውጤት ሪፖርት ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፤

5) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4(ለ) መሰረት በአመልካቹ የቀረበውን ሪፖርት መሰረት በማድረግ ዝርያው ጥቅም ላይ እንዲውል ፍቃድ ይሰጣል።

**7. የአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ዝርያን ስለመልቀቅ**

1) የአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ዝርያን ለማስለቀቅና ለማስመዝገብ የሚያመለክት አመልካች፡-

c) Approves the use of the variety after receiving the information from the applicant.

4/ An applicant who obtains permission according to sub article 3 (b) of this article;

a) Shall carry out the trial in accordance with the variety adaptability trial protocol prepared by the Authority

b) Shall submit a variety adaptation trial result report conducted domestically.

5/ Based on the report submitted by the applicant in accordance with sub article 4 (b) of this article, the Authority shall permit the variety to be used.

**7. Farmers' and semi- pastorals' variety release**

1/ Farmers and semi-pastoralist variety release and registration applicant may be:

ሀ) ለግሉ የሚያስመዘግብ ከሆነ አርሶ አደሩ ወይም ከፊል አርብቶ አደሩ ራሱ ወይም ተወካዩ፣

ለ) በማህበረሰብ ስም የሚመዘገብ ከሆነ በማህበረሰቡ የተወከለ አርሶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር ወይም የአርሶ አደር ድርጅት ወይም የማህበረሰብ ዘር ባንክ ወይም መንግስታዊ የሆነ ድርጅት ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሊሆን ይችላል።

2) አመልካቹ እጩ ዝርያው በሚገኝበት ቀበሌ ላለው የግብርና ጽህፈት ቤት የመጀመሪያ ጥያቄ ያቀርባል፣

3) የቀበሌ ግብርና ጽህፈት ቤት ጥያቄ በቀረበበት ዕጩ የአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ዝርያ ላይ ቀበሌ አቀፍ ቅኝት በማካሄድ ዝርያው በቀበሌው መኖር አለመኖሩን በማረጋገጥ ለወረዳው ግብርና ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያደርጋል፣

4) የወረዳ ግብርና ጽህፈት ቤት ጥያቄ በቀረበበት ዕጩ የአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ዝርያ ላይ ወረዳ አቀፍ ቅኝት በማካሄድ ዝርያው በወረዳው መኖር አለመኖሩን በማረጋገጥ ለዞን

A) The registration application shall be by individual famer or semi pastoralist or the delegate.

b) If registration is going to be in the name of the community, applicant shall be community delegated farmer, semi-pastoralist, community seed bank, institution of a farmer or semi pastoralist, government or non-governmental organization

2/ The applicant submits an initial application to the Kebele agricultural office, where the candidate variety is found.

3/ The Kebele agricultural office reports to the Wereda agricultural office after assessing at the Kebele level for the presence of the candidate variety.

4/ The Woreda agricultural office makes woreda level assessment and reports to the zonal agricultural office whether the presence or absence of the candidate variety

ግብርና ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያደርጋል፣

5) የዞን ግብርና ጽህፈት ቤት ጥያቄ በቀረበበት ዕጩ የአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ዝርያ ላይ ዞን አቀፍ ቅኝት በማካሄድ ዝርያው በዞኑ መኖር አለመኖሩን በማረጋገጥ ለክልል ግብርና ቢሮ ሪፖርት ያደርጋል፣

5/ The zonal agricultural office makes zone level assessment and reports to the regional agricultural office whether the presence or absence of the candidate variety.

6) የክልል ግብርና ቢሮ ጥያቄ በቀረበበት ዕጩ የአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ዝርያ ላይ ክልል አቀፍ ቅኝት በማካሄድ ዝርያው በክልሉ መኖር አለመኖሩን በማረጋገጥ ለግብርና ባለስልጣን ሪፖርት ያደርጋል፣

6/ The regional agricultural office makes regional level assessment and reports to the Authority whether the presence or absence of the candidate variety.

7) ባለስልጣኑ ዕጩ የአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ዝርያ መገኛው ወይም ምንጩ የኢትዮጵያ ስለመሆኑ ወይም በብዝሃ ሕይወት ተለያይነት የኢትዮጵያ ስለመሆኑ ከኢትዮጵያ ብዝሃ ህይወት ተቋም ማረጋገጫ ይጠይቃል፣

7/ The Authority requests the Ethiopian Biodiversity Institute whether the candidate farmer or semi-pastoralist variety is center of origin or center of diversity in Ethiopia.

8) ባለስልጣኑ የአገሪቱ የብዝሃ ሕይወት ተቋም ሪፖርት ሲደርሰው ስለቀረበው ዕጩ ዝርያ ተቃውሞ

8/ The Authority upon receiving the required information from the Ethiopian Biodiversity Institute, invites

ስለአለመኖሩ ሰፊ ሽፋን ባለው መገናኛ ብዙሃን ለ21 ቀናት ጥሪ ያደርጋል፣

9) ዝርያው በሌላ የአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ስለመኖሩ ማረጋገጫ ካልመጣ ባለስልጣኑ ማመልከቻውን በመቀበል በቀረበው ዕጩ የአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ዝርያ ላይ የባህሪ ፍተሻና የብቃት ሙከራ እንዲካሄድ ያደርጋል፣

10)ሆኖም ግን ከሌላ አካባቢ የሚመጣው ማስረጃ ከዕጩ የአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ዝርያ ጋር ተመሳሳይነት ካለው የአመልካቹን በተመሳሳይ የዝርያ ይፈተሽልኝ ጥያቄ ባለስልጣኑ ላይቀበለው ይችላል፣

11)በአቅራቢያ ያለ አግባብ ያለው የመንግስት ተቋም ወይም ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ወይም ምርምር ኢንስቲትዩት ወይም የኢትዮጵያ ብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት የዝርያ ሙከራውን ሊያካሂድ ይችላል፣

the public for any objection to the registration of the candidate local variety in media with wide coverage for duration of 21 days.

9/ The authority upon assuring that the candidate variety is not produced outside the area claimed shall accept the application and allow the national performance trial and distinctness, uniformity and stability test to be carried out.

10/ The Authority may reject the applicant’s request in case there is evidence that shows similarity with the farmers’ or semipastoral’ variety under process.

11/ The nearest and appropriate government institution or higher learning institution, or agricultural research institution or Ethiopian Biodiversity Institute may carry out the variety trial.

12)ሙከራው ባለስልጣኑ በተለይ ለዚሁ ዓላማ በሚያዘጋጀው ቀለል ያለ የባህሪ ልየታና የብቃት ፍተሻ ፕሮቶኮል መሰረት ያካሂዳል፣

13)ባለስልጣኑ ዕጩ የአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ዝርያ በዝርያ ብቃት ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ አማካኝነት ሙከራው እንዲገመገም ያደርጋል፣

14)ሙከራውን ያካሄደው ተቋም የምርት ወቅት ሲጠናቀቅ የሙከራውን ውጤት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

15) የዝርያ አስመዝጋቢው ማህበረሰብ ተወካይ እና ሙከራውን ያከናወነው ተቋም ተወካይ የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ በሚሰጥበት ስብሰባ ወቅት በመገኘት ስለ ዕጩ ዝርያው ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጡ ያደርጋል፣

16)ባለስልጣኑ የዝርያ ብቃት ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ ባቀረበለት ሪፖርት መሰረት በብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፣

12/ The national performance trial and distinctness, uniformity and stability test shall be carried out using a less stringent protocol specifically set for this purpose by the Authority.

13/ The Authority shall perform the trial evaluation using the candidate variety evaluating technical committee.

14/ The institution who carried out the trial shall submit the report to the Authority at the end of the trial period.

15/ The representative of the community who applied for registration of the candidate variety and the representative of the institution who conducted the evaluation shall attend the meeting of the national variety release committee for further explanation of the variety.

16/ The Authority shall make the national variety release committee decision based on the candidate variety evaluating technical committee submitted report.

17) የጸደቀው ዝርያ በተለያየ አመልካች የቀረበ ከሆነ ምዝገባው በሁሉም አመልካቾች ስም ይመዘገባል፣

18)የዝርያ ባህሪ ልየታ ፍተሻ የሰራው አግባብ ያለው የመንግስት ተቋም ከማህበረሰቡ ጋር በመሆን ዝርያውን በማደስ ጠብቆ ማቆየት ይኖርበታል፣

19)ባለስልጣኑ ዕፅዉ የአካባቢ ዝርያ ያለምንም ክፍያ እንዲመዘገብ ያደርጋል።

8. **የዕፅዋት ዓይነቴዎች ልየታ**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ በተደነገገው መሰረት በዝርያ ለቀቃ እና በምዝገባ ሥርዓት የሚያልፉትን የዕፅዋት ዓይነቴዎች ባለስልጣኑ በሚከተለው መስፈርት ይለያል፡-

1) የዝርያ ለቀቃ እና ምዝገባ አሰራርን የተመለከተ ሀገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፋዊ ወይም ቀጠናዊ ስምምነት መሰረት በማድረግ፣

2) ዝርያዎች በገበያው ምክንያት በገበያ ላይ ብዙ ጊዜ ሳይቆዩ በሌላ ዝርያዎች የሚተኩባቸው የዕፅዋት ዓይነቴዎችን ከግምት በማስገባት፣

17/ If the approved variety is submitted by different applicants, the variety shall be registered in the names of all applicants.

18/ The variety shall be maintained by the appropriate institution who carried out the trial together with the community.

19/ The Authority shall register for farmer’s or semi- pastoralist’s variety without charging service fees.

8. **Variety catogorization**

In accordance with the provisions of sub article 2 of article 3 of this directive, the Authority will distinguish the types of plant species that pass for the release and registration system according to the following criteria:

1/ Based on the regional and international agreements ratified by the country regarding the procedures of release and registration of varieties;

2/ Taking into account the types of plants where varieties are quickly replaced by other varieties due to market reasons;

3) የዕፅዋት ዓይነቴዎች ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እና በአርሶ አደሩና በከፊል አርብቶ አደሩ ላይ የሚያደርሱትን ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ ግምት ውስጥ በማስገባት።

**9. በዓይነታቸው ልዩ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ዝርያዎች እንዲመረቱ ስለመፍቀድ**

በዓይነታቸው ልዩ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው፣ የተለዩ እና በውጭ ሀገር የተመዘገቡ የዕፅዋት ዝርያዎች በሀገር ውስጥ የዝርያ ማላመድ ሙከራ ማካሄድ ሳያስፈልግ በቀጥታ እንዲመረቱ ለመፍቀድ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል

1) ሚኒስቴሩ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ የለየውን ዝርያ:-

ሀ) ለውጭ ንግድ መሻሻል፣ ከውጭ የሚመጡ ምርቶችን ለመተካት፣ ለአግሮ ኢንደስትሪ ጥሬ ዕቃ አቅርቦት፣ ለምግብና ስነ-ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚረዳ መሆኑን፣

ለ) በሀገር ውስጥ በበቂ መጠንና ዓይነት አለመኖሩን ሚኒስቴሩ በማረጋገጥ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

3/ Taking into account the national economic importance of plant species and their economic impact on farmers and semi-pastoralists.

**9. Permit the production of plant varieties having a special national significance**

Plants varieties registered in foreign country and identified as having a special national role can be allowed for direct production without conducting adaptation trial in the country with the following criteria:

1/ Variety identified by the Ministry to be imported into the country

a) Ensure its contribution to export trade improvement, import substitution, raw material supply for industry, food and nutrition security;

b) Ensure the variety is not produced in sufficient quantity and type in the country and request the Authority with a written letter.

2) ባለስልጣኑ በሚኒስቴሩ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ የቀረበለትን ማመልከቻ በመመርመርና ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር በ15 ቀናት ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፣

3) ባለስልጣኑ በሚኒስቴሩ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ የተፈቀደው ዝርያ በውጭ ሀገር የተመዘገበና የባህሪ ልዩታ ፍተሻ ሪፖርት መኖሩን ያረጋገጣል፣

4) ከውጭ ሀገር ዝርያ የሚያስገባ አመልካች አስፈላጊው የኳራንቲንና የብዝሃ ህይወት መስፈርት ሟሟላትና ልውጥ ህያው አለመሆኑን ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፤ ዝርያው ልውጥ ህያው ከሆነም አግባብ ካለው መንግስታዊ ተቋም የተፈቀደ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣

5) አመልካቹ ዝርያውን ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው መስፈርት መሰረት በተገለለ ቦታ የብዜት ስራውን ማከናወን አለበት፤

6) አመልካቹ ዘሩን ማስገባት በጀመረ ሁለት ተከታታይ የምርት ወቅት በኋላ ዝርያው እንዲመዘገብለት መጠየቅ አለበት።

2/ The Authority reviews the application in consultation with the Ministry and announces its decision within 15 days.

3/ The Authority assures that the variety requested to be imported is registered outside the country and bears distinctness, uniformity and stability test report.

4/ The applicant needs to ensure the variety fulfills the plant quarantine and biodiversity requirements, if the variety is from foreign sources, and should declare whether the variety is genetically modified oorganism or non- genetically modified oorganism; if it is genetically modified organism, an evidence of permit from the appropriate institution must be submitted to the Authority.

5/ The applicant shall multiply the variety in a protected site based on the criteria set by the Authority.

6/ The applicant, after two consecutive production and importation years of the variety, shall apply for the registration of the variety.

**10. በሀገር ውስጥ ያልተመዘገቡ ዝርያዎችን ከውጪ በማስገባት አባዝቶ መልሶ ወደ ውጪ መላክ**

1) በሀገር ውስጥ ያልተመዘገቡ ዝርያዎች ከውጭ ሀገር አስገብቶ ለማባዛትና መልሶ ለመላክ አመልካቹ የሚከተሉትን መስፈርቶች መሟላት አለበት፡-

ሀ/ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ መሰረት ማመልከት ይኖርበታል፣

ለ/ የግብርና ምርት የማምረት የብቃት እና ወደ ውጭ የመላክ ፍቃድ ሊኖረው ይገባል፣

ሐ/ ስለሚያስገባው ዝርያ ከመነጨበት ሀገር ዝርያው ስለመመዝገቡና ጥቅም ላይ ስለመዋሉ አግባብ ካለው አረጋጋጭ መንግስታዊ አካል ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣

መ/ የሚገባው ዝርያ በሌላ ሀገር ያልተመዘገበ ከሆነ እጩ ዝርያን ለማስመዝገብ የተቀመጠውን የአገሪቱን የምዝገባ ስርዓት ማለፍ ይኖርበታል፣

ሠ/ ስለሚያስገባው ዝርያ ከጭነቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የግዥና የርክክብ ሰነዶችን ማቅረብ ይኖርበታል፣

**10. Importing unregistered variety exclusively for export porpose**

1/ The following requirements must be met by the applicant to import and multiply unregistered varieties in the country for rexport pourpose:

a) Shall apply according to the application form prepared by the Authority;

b) Shall have competence ceretificate to produce and a license to export agricultural products;

c) Shall submit evidence that shows the imported variety has been registered and used somewhere else from the appropriate verifying governmental body in the country of origion.

d) If the variety is not registered in any other country, the candidate shall go through the country's registration system to be registered.

e) Shall provide purchase and delivery documents related to the shipment.

ረ/ ዝርያው ልውጥ ህያው አለመሆኑን፤ ከሆነም አግባብ ካለው ተቋም የተፈቀደ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣

2) ባለስልጣኑ የአመልካቹን ጥያቄ በመመርመር አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ የማስገቢያ ፍቃድ ይሰጣል፡፡

3) አመልካቹ ያስገባውን ያልተመዘገበ ዝርያ የሚያባዛበትን ቦታ በግልጽ ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ማሳወቅ እና በተገለለ ቦታ ላይ ማምረት ይኖርበታል፡፡

4) ባለስልጣኑ ወደ ሀገር ውስጥ የገባውን ያልተመዘገበ ዝርያ ሰነድ ይመረምራል፣ ለታለመለት ዓላማ ብቻ እየዋለ መሆኑን በመስክ ክትትል ያደርጋል፡፡

5) ቁጥጥር በሚደረግበት ወቅት በባለስልጣኑ የሚሰጠውን ምክረ-ሀሳብ አመልካቹ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

6) አመልካቹ ያስገባውን ዝርያም ሆነ ከዝርያ የሚገኝን ምርት እንዲሁም ተረፈ ምርት፡-

f) Shall declare the variety is non-genetically modified organism, if it is genetically modified organism, an evidence of permit from the appropriate institution must be submitted to the Authority.

2/ When the Authority reviews the applicant's request and meets the necessary requirements, shall issue an import permit.

3/ The applicant must clearly inform the Authority of the production place of the unregistered variety and must produce it in a protected area.

4/ The Authority examines the document of the unregistered variety imported into the country and conducts field monitoring to ensure that it is being used only for its intended purpose.

5/ The applicant should fully implement the recommendations given by the Authority during inspection.

6/ The imported variety introduced by the applicant, its product and the by-products:

ሀ) ሌላ ወገን እንዲጠቀምበት ወይም ገበያ ላይ እንዲያውል ወይም በሽያጭም ሆነ በስጦታ አሳልፎ መስጠት አይችልም፣

ለ) ከታለመለት ዓላማ ውጭ ተጠቅሞ ቢገኝ ተጠያቂ ግድታ መግባቱን በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፣

ሐ) በዝርያው ምክንያት ለሚደርስ ማንኛውም ጉዳት ኃላፊነቱን በመውሰድ ካሳ መክፈል አለበት፤

7) ዝርያውን ለሁለተኛ ዙር ለማስገባት አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ በመጀመሪያው ዙር ከተላከው የምርት መጠን የተገኘውን የውጪ ምንዛሬ መጠን የሚያሳይ መረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 11. እጩ ዝርያ ስለመመዝገብ

1) አመልካቹ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ዝርያው እንዲመዘገብለት መጠየቅ አለበት፣

2) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ወይም 5 በተደነገገው መሰረት በብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ እንዲለቀቅ ወይም እንዲመዘገብ ውስኔ የተሰጠበትን ዝርያ እና

a) Can not hand it over to another party for use or market either by sale or gift.

b) Shall submit a written commitment contract that shows taking accountability not to use outside of the intended purpose.

c) Shall take the responsibility for any damage caused by the variety and pay compensation.

7/ In order to import the variety for the second round, information showing the amount of foreign currency obtained from the quantity of the product sent in the first round, verified by the relevant body, should be submitted.

## 11. Registration of candidate variety

1/ The applicant shall fill in the application form prepared by the Authority and pay service fee to request the variety to be registered.

2/ Based on the provisions of article 4 or 5 of this directive, the Authority shall register the released and registered varieties ratified by the national variety release committee and in accordance with the international

ሀገሪቱ አባል በሆነችባቸውና ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት በብሔራዊ ዝርያ መዝገብ ይመዘግባል፣

3) ማንኛውም ዝርያ ሲመዘገብ መለያ ስያሜ ሊሰጠው ይገባል፣

4) ባለስልጣኑ የዝርያውን ስም፣ የአስመዝጋቢውን ስም እና የአዳቃዩን ስም መዝግቦ መያዝ አለበት፣

5) ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተደነገገው በአለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት ለሚመዘገቡ ዝርያዎች አመልካቹን የዝርያ ልየታ ፍተሻ እና የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ ሰነድ ቅጂ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

6) የጸደቀው ዝርያ በተለያዩ አመልካቾች በእኩል ጊዜ የቀረበ ከሆነ ምዝገባው በሁሉም አመልካቾች ስም ይሆናል፡፡

7) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ዝርያው የአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ዕፀዉ የአካባቢ ዝርያ ከሆነ ያለምንም ክፍያ እንዲመዘገብ ያደርጋል።

agreements to which the country is a member.

3/ When any variety is registered, naming is a must to be identified.

4/ The Authority shall record the name of the variety, the name of the registrant and the name of the breeder.

5/ When the Authority deems it necessary, as it is stated in sub article 2 of this article for varieties will be registered in accordance with the international agreemment, it may ask the applicant to submit a copy of the national performance trial and the distinctness, uniformity and stability report of the variety.

6/ If the approved variety is presented by different applicants at the same time, the registration will be done by all applicants' name.

7/ Without prejudice to this article sub article 1, if the variety is a local variety of farmers or semi-pastoralists, it will be registered free of charge.

**12. የዝርያ ስያሜ**

1) ባለስልጣኑ በአመልካቹ የቀረበውን የዝርያ ስያሜ የሚከተሉት መስፈርቶች ከግምት ውስጥ መግባታቸውን በመገምገም ውሳኔ ይሰጣል።

የዝርያ ስያሜ:-

ሀ) አጭርና ግልጽ መሆን አለበት፣

ለ) በቁጥር ብቻ መገለጽ የለበትም፣

ሐ) ከዝርያው ባህሪ ጋር ያልተያያዘ መሆን አለበት፣

መ) የማህበረሰብን እሴትና ባህል የማይጻረር መሆን አለበት፣

ሠ) በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በሌላ ሀገር ቀደም ብሎ የተሰጠን መብት መጉዳት የለበትም፣

ረ) ከማንኛውም የዕፅዋት ዝርያ ስያሜ ጋር አሳሳች መሆን የለበትም።

2) በአመልካቹ የቀረበው የዕፅዋት ዝርያ ስያሜ በዚህ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን መስፈርት ካላሟላ ባለስልጣኑ ለአመልካቹ በ15 ቀናት ውስጥ ተለዋጭ ስያሜ እንዲያቀርብ በጽሁፍ ያሳውቃል፣

**12. Variety Naming**

1/ The Authority shall give a decision on the proposed variety name by the applicant taking into consideration the following criteria;

Variety name:

a) Shall be short and clear;

b) Shall not be expressed in numbers only;

c) Shall not be directly associated with the characters of the variety;

d) Shall not undermine the values and cultures of societies;

e) Shall not cause damage to previously granted rights in Ethiopia or in any other country;

f) Shall not be misleading with other variety names.

2/ The Authority shall inform the applicant to submit an alternative name within 15 days if the proposed name submitted by the applicant is not compliant with the provisions of article 12 sub article 1 of this directive.

3) አመልካቹ የዝርያ ስያሜ ለውጥ ለማድረግ ሲፈልግ ለባለስልጣኑ ማመልከት ይችላል፤ ባለስልጣኑም በዚህ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት ጥያቄው አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው የዝርያ ስያሜ ለውጡን ተቀብሎ ይፈቅዳል፣

4) ባለስልጣኑ የተመዘገበውን የዝርያ ስያሜ አግባብነት የሌለው መሆኑን በሂደት ከደረሰበት አመልካቹ ተለዋጭ ስያሜ እንዲያቀርብ በማድረግ ስያሜ እንዲቀየር ያደርጋል።

**13. ዝርያን ከዝርያ መዝገብ ስለመሰረዝ**

1) ባለስልጣኑ በተለያየ ምክንያት ከመመረት ውጪ የሆኑ ዝርያዎችን በሚከተሉት ምክንያት ሊሰርዝ ይችላል፡-

ሀ) ዝርያውን ያስመዘገበው ተቋም ዝርያውን በአግባቡ ጠብቆ ማቆየት አለመቻሉ ሲረጋገጥ፣

ለ) ዝርያው ሲመዘገብ የነበረውን ብቃት ወይም ባህሪ ማጣቱ ሲረጋገጥ፣

ሐ) የዝርያው አስመዝጋቢው

3/ The applicant may submit request to the Authority to change the variety name; the authority shall approve the request after ensuring the requirements under article 12 sub article 1.

4/ The Authority may force the applicant to change the name of the variety, if the Authority finds out that the registered variety got the name inappropriately.

**13. Delisting variety from the national registration book**

1/ The Authority may delist varieties that become obsolete based on the following reasons :-

a) When the registrant could not maintain the variety appropriately;

b) When the variety loses the performance or the character that the variety possessed during registration;

c) When the breeder requests the

ዝርያው እንዲሰረዝ ሲጠይቅና የጠየቀበት ምክንያት ባለስልጣኑ አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው፣

መ) ዝርያውን በተጠቃሚዎችና በአምራቾች ለመጠቀም ፍላጎት የማይኖር እንደሆነ ሲረጋገጥ፣

ሠ) ዝርያው የተመዘገበው በስህተት መሆኑ በማንኛውም ጊዜ ሲረጋገጥ፣

2)እንዲሰረዝ የተደረገ ዝርያ ናሙና በባለስልጣኑ ወይም በብዝሃ ህይወት ማቆያ መቀመጥ ይኖርበታል።

3)ዝርያው ከዝርያ መዝገብ ከተሰረዘ በኋላ የተሰረዘበት ምክንያት በበቂ ሁኔታ ካልሆነና ይህም በጥናት ከተረጋገጠ ባለስልጣኑ ወደ ዝርያ መዝገብ ሊመልሰው ይችላል።

Authority to delist the variety, and the Authority finds the reason for delisting is acceptable.

d) When the Authority confirms that there is no interest in using the variety by the producers and users.

e) When the variety registration was found illegitimate at any time.

2/ Sample of the delisted variety shall be deposited in storage facilities of the authority or the Ethiopian Biodiversity Institute.

3/ A deleted variety may be reinstated to the national registration book by the authority; if the deletion was affected erroneously and supported by the study conducted.

## ክፍል ሦስት

## የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ እና የቴክኒካል ኮሚቴዎች

### 14. ስለ ብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ

1) በአዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 8 በተደነገገው መሰረት ዕጩ ዝርያዎችን እና ከመመረት ውጭ በሆኑ ዝርያዎች ላይ ውሳኔ የሚሰጥ ገለልተኛ የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል።

2) የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ አባላት ስብጥር ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ባለድርሻ አካላት የሚወከል ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ከሌሎች ተቋማት እና የህብረተሰብ ክፍሎች ሴቶች ወይም ወጣቶች ወይም አርሶ/አርብቶ አደሮች የሚወከል አባል ሊኖረው ይችላል።

   ሀ) ከግብርና ሚኒስቴር
   ለ) ከኢትዮጵያ ዘር አሶሴሽን
   ሐ) ከኢትዮጵያ ብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት
   መ) ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት
   ሠ) ከክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት
   ረ) ከዩኒቨርሲቲ

## Section Three

## National Variety Release Committee and Technical Committees

### 14. The national variety release committee

1/ According to the Proclamation article 4 sub article 8, a neutral national variety release committee responsible to approve registration and decision on varieties to be deleted is established by this directive.

2/ Membership of the national variety release committee shall be representatives drawn from the following; but may also have additional representatives from other institutions and from social groups, including women, youth, farmers, and pastoralists.

   a) Ministry of Agriculture
   b) Ethiopian Seed Association
   c) Ethiopian Biodiversity Institute
   d) Ethiopian Institute of Agricultural Research
   e) Regional Agricultural Research Institute
   f) University

ሰ) ከገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር ዩኒየን

ሸ) ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት

ቀ) ከኢትዮጵያ ግብርና ምርት አቀናባሪዎች አሶሴሽን

በ) ከኢትዮጵያ ደን ልማት

ተ) ከኢትዮጵያ ጥራጥሬዎች፣ ቅባት እና ቅመማ ቅመም እህል አቀናባሪዎችና ላኪዎች ማህበር

ቸ) ከኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር አምራቾችና ላኪዎች ማህበር

ኀ) ከኢትዮጵያ መኖ ዘር አሶሴሽን

ነ) ከኢትዮጵያ ዕፅዋት ጥበቃ ባለሙያዎች ማህበር

ኘ) ከባለስልጣኑ የዝርያና ዘር ሬጉላቶሪ ሃላፊ (ቋሚ ጸኃፊ)

አ) እንደስፈላጊነቱ ተጨማሪ ሌሎች ተቋማትን ሊያካትት ይችላል፡፡

3) ባለስልጣኑ ለግምገማ የሚጠሩ አባላትን እንደሚገመገመው የዕፅዋት ዓይነት ይወስናል።

4) የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ አደረጃጀት

ሀ) ኮሚቴው ሰብሳቢና ጸኃፊ ይኖረዋል፣

ለ) ሰብሳቢው ከብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ አባላት መካከል

g) Farmers Cooperative Unions

h) Ethiopian Public Health Institute

i) Ethiopian Agricultural products Processors Association

j) Ethiopian Forest Development

k) Ethiopian Pulses Oil Crops and Species Processors Exporters Association

l) Ethiopian Horticulture Producer Exporters Association

m) Ethiopian Forage Seed Association

n) Plant Protection Society of Ethiopian

o) The Ethiopian Agricultural Authority Variety and Seed Regulatory head (Permanent secretary)

p) Other institutes shall be included as deemed.

3/ The Authority shall decide the participation of members based on the type of plant species to be evaluated.

4/ Organization of the national variety release committee

a) The national variety release committee shall have chairperson and secretary

b) The chairperson shall be designated by the Authority from the members of the national variety release committee

በባለስልጣኑ ይሰየማል፣

ሐ) እንደአስፈላጊነቱ አሰራሩን ለማሳለጥ ውስጠ ደንብ ሊያዘጋጅ ይችላል።

5) የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

ሀ) የዕጩ ዝርያ ብቃት እና ባህሪ ፍተሻ ሪፖርት እና በዝርያ ብቃት ግምገማ ቴክኒካል ኮሚቴ የሚቀርብለትን ሪፖርት ይቀበላል፣ ይገመግማል፣

ለ) የቀረበው ሪፖርትን እና እንደአስፈላጊነቱ የአመልካቹን ምላሽ በመገምገም ውሳኔ ያሳልፋል። ውሳኔውም ዝርያው ሙሉ በሙሉ እንዲጸድቅ ወይም በጊዜያዊነት እንዲጸድቅ ወይም የዝርያ ብቃት እና ባህሪ ፍተሻ ጥናቱ እንዲደገም ወይም እንዲወድቅ ሊሆን ይችላል፣

ሐ) ከመመረት ውጭ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎችን ከሚገመግም ቴክኒካል ኮሚቴ በሚቀርብለት ሪፖርትና ምክረ - ሃሳብ መሰረት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

c) As deemed necessary, the national variety release committee may prepare an internal working procedure to facilitate its duties.

5/ The national variety release committee shall have the following powers and duties:

a) Receives and evaluates the candidate’s variety performance and distinctness, uniformity and stability report from candidate variety evaluating technical committee.

b) Based on the report and as appropriate listening to the response of the applicant, the national variety release committee gives decision. The decision may be to approve, or to provisionally approve, or to reject or to repeat the performance test and the distinctness uniformity and stability test.

c) Gives final decision based on the recommendation and reports submitted by the obsolete variety evaluating technical committee.

6) የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ አሰራር

ሀ) ዕጩ ዝርያዎች ላይ ውሳኔ ለመስጠት በዓመት ሁለት የስብሰባ ጊዜ ይኖረዋል፣

ለ) ስብሰባውን ለማካሄድ ጥሪ ከተደረገላቸው አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ ሊገኙ ይገባል፣

ሐ) በቀረበው ዕጩ ዝርያ ላይ በስብሰባው ከተገኙት ውስጥ ቢያንስ የ2/3ኛውን የድጋፍ ድምጽ ሲያገኝ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፣

መ) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሰብሳቢው በማይገኝበትና መወከል በማይችልበት ወቅት ጸሃፊው ከአባላቱ መካከል በጊዜያዊነት ሰብሳቢ ይመድባል።

7) የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) ከጸሃፊው ጋር በመመካከር የስብሰባ ቀናትን ይወስናል፣ አጀንዳ ይቀርጻል፣

ለ) ከጸሃፊው ጋር በመመካከር ለውሳኔ መጠራት ያለባቸውን የኮሚቴ አባላት አስቀድሞ ያሳውቃል፣

ሐ) የኮሚቴ ተግባራትን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣

6/ Working procedures of the national variety release committee

a) Shall have two meetings in a year to decide on candidate varieties

b) To reach a quorum attendees shall be above 50% of the invited members.

c) A variety shall be approved if 2/3 of the participants support the decision.

d) The secretary shall designate a temporary chairperson from the members of the national variety release committee, when the chairperson is abscent and can not delegate anyone.

7/ Powers and duties of the national variety release committee chairperson

a) Sets date and agenda of the meeting in consultation with the secretary;

b) In consultation with the secretary, informs the participants who should participate in the meeting for decision;

c) Leads and coordinates the national variety release committee tasks;

መ) ዝርያ ለቀቃ እና ምዝገባን በተመለከተ ኮሚቴውን ይወክላል።

8) የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ጸሃፊ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) የስብሰባ ቃለ-ጉባዔ ይይዛል፣ መረጃን ያደራጃል፣

ለ) ከሰብሳቢ ጋር በመመካከር የስብሰባ ቀናትን ይወስናል፣ አጀንዳ ይቀርጻል፣

ሐ) በቀረቡት ዝርያዎች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ለባለስልጣኑ ሪፖርት ያደርጋል።

9) የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ አባላት የአገልግሎት ዘመን

ሀ) የአንድ ዙር የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት ሲሆን አንድ አባል ከሁለት የአገልግሎት ዘመን በላይ ማገልገል አይችልም፣

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 ፊደል (ሀ) የተደነገገው በጸሃፊው ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፣

ሐ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብሳቢው ለተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲያገለግል ሊደረግ ይችላል፣

መ) አንድ የኮሚቴ አባል ሲለቅ በተወከለበት ተቋም እንዲተካ ይደረጋል።

d) Represents the national variety release committee regarding variety release and registration.

8/ Powers and duties of the national variety release committee secretary

a) Keeps the minutes of the meeting and organizes information

b) Sets date and agenda of the meeting in consultation with the chairperson

c) Submits report to the Authority on the varieties that received the decision.

9/ Term of service of the national variety release committee

a) One term service is three years; one member cannot serve for more than two terms

b) The provision in this article sub article 9 (a) shall not be applicable to the secretary of the national variety release committee.

c) As deemed necessary the chairperson may be allowed to serve for an additional one year.

d) When any member leaves membership of the committee, membership replacement shall be effected from the institution that delegated the initial member.

**15. ስለ ዕጩ ዝርያዎች ብቃት ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ**

1) በአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 8 ፊደል (ሀ) በተደነገገው መሰረት የዕጩ ዝርያን ብቃት የሚገመግም ቴክኒካል ኮሚቴ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፣

2) ባለስልጣኑ ለአንድ የምርት ወቅት ብቻ የሚያገለግል የሚከተሉትን ባለሙያዎች ያካተተ የዕጩ ዝርያዎች ብቃት ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ ያዋቅራል።

ሀ) የዕፅዋት አዳቃይ (ቡድን መሪ)፣
ለ) የዕፅዋት ጥበቃ ባለሙያ፣
ሐ) አግሮኖሚስት ወይም ሆርቲካልቸሪስት፣
መ) እንደአስፈላጊነቱ ሌላ ተጨማሪ ባለሙያ ሊያካትት ይችላል።

3) የዕጩ ዝርያዎች ብቃት ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለባለስልጣኑ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል።

ሀ) የዕጩ ዝርያን ብቃት በመረጃ፣ በመስክ ምልከታና የተጠቃሚዎችን ፍላጎት እና አስተያየት መሰረት በማድረግ ይገመግማል፣

**15. The candidate variety evaluating technical committee**

1/ A candidate variety evaluating technical committee, responsible for evaluating the performance of candidate variety, is hereby established by this directive in accordance with article 4 sub article 8 (a) of the proclamation.

2/ The Authority shall organize a candidate variety evaluating committee members that serve for one year with the following composition:

a) Plant breeder (team leader);

b) Plant protection expert;

c) Agronomist or horticulturist;

d) Other experts as deemed necessary

3/ The candidate variety evaluating committee being accountable to the Authority shall have the following powers and duties:

a) Evaluates candidate variety using data, field visit, customer’s preference and suggestions

ለ) የግምገማውን ውጤት እና ምክረ-ሃሳብ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ያቀርባል፣

ሐ) የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ለውሳኔ በሚሰበሰብበት ወቅት የቴክኒካል ኮሚቴው ቡድን መሪ ወይም የኮሚቴው አባል ስለ ግምገማው ውጤትና ምክረ-ሃሳብ ማብራሪያ ያቀርባል።

**16. ከመመረት ውጭ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎችን የሚገመግም ቴክኒካል ኮሚቴ**

1) በአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 8 ፊደል (ለ) በተደገገው መሰረት ከመመረት ውጭ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎችን የሚገመግም ቴክኒካል ኮሚቴ በዚህ መመሪያ በባለስልጣኑ ተቋቁሟል፣

2) ከመመረት ውጭ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎችን የሚገመግም ቴክኒካል ኮሚቴ ከሚከተሉት ተቋማት የተወጣጡ አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ከግብርና ሚኒስቴር፣

ለ) ከግብርና ባለስልጣን፣

ሐ) ከግብርና ምርምር እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣

b) Submits the evaluation result and recommendations written to the Authority,

c) The team leader of the candidate variety evaluating technical committee or any of the members of the committee shall attend and explain the result of the evaluation and recommendations at the meeting of the national variety release committee convening to decide on the variety.

**16. Obsolete plant variety evaluating technical committee**

1/ An obsolete variety evaluating technical committee responsible for evaluating the obsolete variety is hereby established by this directive, in accordance with article 4 sub article 8 (b) of the proclamation.

2/ The obsolete variety evaluating technical committee shall have members from the following institutions

a) Ministry of Agriculture

b) Ethiopian Agricultural Authority

c) Ethiopian Agricultural Research and Higher Learning Institutions

መ) ከዘር አምራቾች ወይም ማህበራት፣

ሠ) እንደአስፈላጊነቱ ከሌሎች ተቋማት።

3) የቴክኒካል ኮሚቴው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መረጃዎችን ከባለስልጣኑ እንዲቀርብለት ያደርጋል፡-

ሀ) ከአስመዝጋቢው የቀረበ የይሰረዝልኝ ጥያቄ፣

ለ) የዝርያው ባህሪ እና ብቃት፣

ሐ) በመደበኛው የዘር ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ውስጥ ያላለፈ ስለመሆኑ ሪፖርት፣

መ) ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች።

4) ከመመረት ውጭ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎችን የሚገመግም ቴክኒካል ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለባለስልጣኑ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል።

ሀ) በባለስልጣኑ ከመመረት ውጭ እንዲሆኑ የተለዩ የዕፅዋት ዝርያዎች ላይ መረጃዎችን በማሰባሰብ ግምገማ ያካሂዳል፣

ለ) የግምገማውን ውጤትና ምክረ-ሃሳብ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ያቀርባል፣

ሐ) እንደአስፈላጊነቱ ከመመረት ውጭ

d) Seed Producers or Association

e) As deemed necessary from other institutions

3/ The obsolete variety evaluating technical committee requests the following information from the Authority

a) Application from the registrant requesting delisting of the variety;

b) Report on the variety characters and, performance

c) The report stating that the status of the variety in the formal quality control system

d) Any other related information.

4/ The obsolete variety evaluating technical committee being accountable to the Authority shall have the following powers and duties:

a) Evaluates the varieties identified by the Authority for delisting through collecting data.

b) Submits the evaluation result and recommendations in written to the Authority,

c) As deemed necessary, the obsolete

የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎችን የሚገመግም ቴክኒካል ኮሚቴ ለብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ማብራሪያ እንዲሰጥ ይደረጋል።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

17. አንድ አመልካች በአንድ ወቅት የሚያቀርበውን የእጩ ዝርያ ብዛት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ባለስልጣኑ ሊወስን ይችላል፡፡

18. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

1) የዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ሙሉ ለሙሉ ተፈጻሚ የሚሆነው
   ሀ) ቀደም ሲል የተጀመሩ ሙከራዎች ሂደታቸውን ሲጨርሱ፣
   ለ) ባለስልጣኑ በሰው ሃይል፣ በመሞከሪያ ቦታ እና በቁሳቁስ በሚገባ ከተደራጀ በኋላ ለእያንዳንዱ በሰብል ዓይነት ስርዓቱን መጀመሩን በድህረ ገጹ ወይም በሌሎች መገናኛ ዘዴዎች ሲያሳውቅ ነው፡፡

variety evaluating technical committee would be required to present explanation to the national variety release committee.

## Section Four
## Miscellaneous Provisions

17. The maximum number of candidate varieties applied for a season shall be determined by the Authority considering the existing condition.

18. **Transitional Provisions**

1/ The provisions of article 4 of this directive shall be fully implemented;
   a) When the previously started experiments have finished;
   b) When the Authority is well capacitated in terms of human resources, testing sites, and equipment; and has announced the start of the system for each type of crop through its website or other means of communication.

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የተደነገገው ቢኖርም ባለስልጣኑ የዝርያ ብቃት እና የባህሪ ልየታ ፍተሻ ሙከራ ከሌሎች ተቋማት ጋር በትብብር ሊሰራ ይችላል፡፡

**19. ስለ ተሻረ መመሪያ**

በሀገር ውስጥ ያልተመዘገቡ ዝርያዎች ከውጭ አስገብቶ የማባዛትና መልሶ ለመላክ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 456/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

**20. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ድንጋጌዎች**

ጥራቱ የተገለጸ ዘር ስርዓት ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 839/2007 አንቀጽ 9 ዝርያ ስለማስመዝገብ የተደነገገው በዚህ መመሪያ መሰረት ተፈጻሚነት አይኖረውም።

**21. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በግብርና ሚኒስቴር ድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)
የግብርና ሚኒስቴር
ሚኒስትር

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article 1(b) of this article, the Authority shall implement the national performance trial and distinctness, uniformity and stability test in collabration with other institutions.

**19. Repealed Directive**

Multiplying and Re-exporting of Imported and Locally Unregistered Variety Implementation Directive Number 456/2021 is repealed by this directive

**20. Inapplicable provisions**

Quality Declared Seed Implementation Directive Number 839/2015 article 9 that provides variety registration is not applicable based on this directive

**21. Date of enforcement of this directive**

This Directive shall enter into force as of the date of its registration by the Ministry of Justice and its uploading on the official website of the Ministry of Finance.

Girma Amente (PhD)
Ministry of Agriculture
Minister